MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ROCKVILLE, MARYLAND

# ሁሉም ማለት ሁሉንም ነው

የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተልእኮ ሁሉም ተማሪ በኮሌጅ፣ በሥራ፣ እና በማህበረሰቡ ዘንድ በወገንተኝነት ያልሆነ ስኬታማ ለመሆን የሚያስችሉት/የሚያስችላት የአካደሚክ፣ፕሮብሌሞችን/ችግሮችን የመፍታት የፈጠራ ችሎታ፣ እና ማህበራዊ እና ስሜታዊ ክህሎቶች እንዲኖሩት/እንዲኖሯት ማረጋገጥ ነው። በርካታ ተማሪዎቻችን በከፍተኛ ደረጃ ስኬታማነትን እየተጎናጸፉ ቢሆንም፣ ብዙዎች ግን ይሄን ዕድልና ድጋፍ እንዲሁም ያላቸውን እምቅ አቅም በቁምነገር ለመጠቀም የሚያስችላቸው መገልገያ ግብአቶችን አያገኙም፣ በተማሪዎች ስኬታማነት ላይ በሁሉም የመማሪያ ክፍሎች፣ እና በሁሉም ት/ቤቶቻችን ያለውን አለመመጣጠን/የልዩነት ክፍተቶችን ለመዝጋት የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በቁርጠኝነት ይሰራል።

## እኛ ማን ነን

## 2018-2019 የተማሪዎች ስብጥር

ሂስፓኒክ/ላቲኖ (Hispanic/Latino) 31.3%

ነጭ (White) 27.7%


ጥቁር አፍሪካዊያን አሜሪካውያን (Black or African American) 21.6%

ኤዥያን (Asian) 14.3%

አገር በቀል ሐዋያን ወይም ከሌላ የፓስፊክ ደሴቶች (Native Hawaiian or other Pacific Islander) ≤5

አሜሪካውያን ኢንድያን ወይም የአላስካ ተወላጅ (American Indian or Alaskan Native) ≤5

ሁለት ወይም የበለጠ ዘር (Two or more races) ≤5




**ጠቅላላ ተማሪዎች፡- 162,680**

አንደኛ ደረጃ (Elementary) (K–5): 76,275


መካከለኛ ደረጃ/Middle (6–8): 36,489

ሁለተኛ ደረጃ/High (9–12): 49,315

ተለዋጭ ፕሮግራሞች/ልዩ ትምህርት ቤቶች 601


## አገልግሎቶች

2018-2019





## በዩናይትድ ስቴትስ14ኛትልቁ የትምህርት ሥርአት

በሜሪላንድ ትልቁ



## ተማሪዎች ከ157የሚበልጡ አገሮች

150 ቋንቋዎችን የሚናገሩ



# እድሎችን ማስፋፋት
# እና የወደፊት አቅምን ማዳበር



## እድሎችን ማስፋፋት

**የመጠቀሚያ መብት መንገድ/ዘዴ ማግኘት ስኬትን/ክንዋኔን ይቀድማል። ለዚህ ነው MCPS ለሁሉም ተማሪዎች የመማር ጥራትን በማሻሻል የተረጋገጠባቸውን የተለያዩ ዓይነት በርካታ የትምህርት ፕሮግራሞችን የማግኛ መንገዶችን ለማስፋፋት እና የትምህርት ጊዜ ለመጨመር በቁርጠኝነት የሚሰራው።**

ቋንቋ፣ ማንበብና መጻፍ የማሻሻያ እድሎች ተስፋፍተዋል። ከመደበኛው የቋንቋ ጥልቀት ፕሮግራሞች በተጨማሪ፣ በአሁኑ ወቅት MCPS *ሁለት-አቅጣጫ የቋንቋ ጥልቀት ፕሮግራሞች (immersion programs)* በአካባቢ ት/ቤት አሉት። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ያሉ ተማሪዎች 50 ፐርሰንት ትምህርት የሚያገኙት በእንግሊዝኛ እና 50 ፐርሰንት ትምህርታቸውን በሌላ የትኩረት ቋንቋ ይሆናል። MCPS በተጨማሪም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነትን ለማዳበር በተጨማሪ የመማሪያ ቦታ እና ሁሉአቀፍ

ማጣራት እና ተጨማሪ የአካባቢ ትምህርት ቤቶችን በማዳበር ሁሉም ተማሪዎች፣ በዚፕ ኮድ ሳይገደቡ ፕሮግራሙን እንዲሳተፉ ለማስቻል ነው።

የመማሪያ ጊዜን ማራዘም ትርጉም ያለው ተጨማሪ የማስተማር ጊዜ የትምህርት ክስረትን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን፣ የተማሪ ውጤቶችን እንደሚያሻሽልም መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ በተለይም በድህነት ተፅእኖ ውስጥ ለሚገኙ ቤተሰቦች፣ ይበልጡኑ ደግሞ ሰመር ላይ ለመማር ያልቻሉትን ይጠቅማል። የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ይህንን ለመፋለም፣ አሁን ያሉትን የሰመር ፕሮግራሞችን የተደራሽነት እና የማስተማሪያ ጊዜ እያስፋፉ ነው (ELO SAIL, ELO STEP and the BELL program) እና በጁላይ 2019፣ MCPS የትምህርት ዓመቱን በሁለት የምድብ I የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች (Roscoe R. Nix and Arcola) ላይ በ30 ቀናት ያራዝማል።

ቀደም ብሎ ትምህርት መጀመር/ቀደም ብሎ ለትምህርት መጋለጥ የትምህርትን ጉዞ ለመጀመር በጣም ቀደመ/ፈጠነ የሚባል ነገር አይደለም። በትንሽነት የህፃንነት እድሜ የመማር እድል ያገኙ ተማሪዎች በአጭር ጊዜ እና በረዥም ጊዜ የበለጠ ውጤታማ ለመሆን እንደሚችሉ የምርምር ውጤቶች ያመለክታሉ። የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እነዚህን ቀደም ብሎ ትምህርት የመጀመር እድሎችን እየሰጠ ነው።የ Pre-K ክፍሎችን በማስፋፋት እና ሙሉ ቀን የመማር ተሞክሮዎችን በመጨመር ጠቅላላ በካውንቲው ውስጥ ድህነት ለተጫናቸው በርካታ ተማሪዎች የሳይንስ፣ ኢንጅነሪንግ፣ ቴክኖሎጂ እና የሂሳብ/Science, Engineering, Technology and Math (STEM) እድሎችን ወደ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ዋና ሥርዓተ ትምህርት ላይ

## የታመቀ ችሎታ እንዲለቀቅ ማድረግ

**ለተማሪዎቻችን እኛ ያለብን ሃላፊነት ት/ቤቶቻችንን በሚለቁበት ወቅት ለወደፊታቸው ትርጉም ያለው አማራጮችን ይዘው እንደሚለቁ ማረጋገጥ ነው። እነዚህ አማራጮች ክሬዲት-የሚያስገኙላቸው የኮሌጅ ኮርሶች፣ ትርጉም ያለው ሥራ ለመጀመር ተፈላጊ የሆኑ የሙያ እውቀት እና የሙያ ፈቃዶችን መያዝ፣ ወይም ለአብዛኛዎቹ ተማሪዎቻችን ሁለቱንም ሊሆን ይችላል።**

ለትክክለኛና ጥብቅ የኮርስ ስራዎች የኮሌጅ ግምገማ መሰናክሎችን መስበር ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ተማሪዎች ጥረትና ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ትምህርት ሲጋፈጡት እና ድጋፍ ሲያገኙ እስከ ክብረወሰን ይመጥቃሉ። የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የከፍተኛ ደረጃ ምደባ/አድቫንስድ ፕሌስሜንት (AP) እና *ኢንተርናሽናል ባስሎሪት/International Baccalaureate (IB)* ኮርሶችን በተለይም ብዙ ተጠቃሚ ያልሆኑ የተማሪ ቡድኖች ላይ በማተኮር ሁሉም ተማሪዎች ትክክለኛና ጥብቅ የኮርስ ስራዎችን የመሳተፍ እድል እንዲኖራቸው ማስቻል። በተጨማሪም ሁሉም የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ፈተናዎችን የመሥራት (SAT፣ ACT ወይም Career Certificates) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የሚኖራቸውን እቅድ ለመደገፍ ሥራ እና ማህበረሰብ ዝግጁነት ከሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መሠረታዊ ኃላፊነቶች አንዱ ተማሪዎቻችንን ለወደፊቱ የሥራ ግብረሃይል መሪዎች እንዲሆኑ ማዘጋጀት ነው። የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለሥራ-ዝግጁነት የሚሰጡ ኮርሶችን ጥራት አሻሽሏል እናም አስፋፍቷል። ፕሮግራሞቹ ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ከኢንጅነሪንግ እስከ አቪየሽን፣ ፋይናንስ እና የማስተማር ሥራ ይለያያሉ። አንዳንድ ፕሮግራሞች የሚሰጡት የሁለት-ዓመት አሶሽየት ዲግሪ ተማሪዎቹ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሚመረቁበት ጊዜ ምንም ወጪ ሳያስከትልባቸው ወይም በአነስተኛ ወጪ የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በተጨማሪ እያስፋፋ የሚገኘው ለሥራ ዝግጁነት

### የአካል፣ ማህበራዊ፣ እና ስነልቦናዊ ደህንነት

ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ደረጃ የአካደሚክ ጥናት እንዲደርሱ፣ ለመማር የሚያዘጋጇቸውን የአካል፣ ማህበራዊ፣ እና ስነልቦናዊ ድጋፎች እንዲኖሯቸው ያስፈልጋል። የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዚህ ረገድ ትርጉም ያለው ኢንቨስትመንት ማድረጉን ይቀጥላል።

እነዚህ ኢንቨስትመንቶች የሚያካትቱት፡-

» የሙሉ ጊዜ ካውንስለሮችን በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች መጨመር፣

» በት/ቤቶች የስነልቦናዊ/ሳይኮሎጂያዊ አገልግሎቶችን በተጨማሪ መመደብ፣

» በጠቅላላ በካውንቲው ውስጥ የአእምሮ ጤንነት ፕሮግራሞችን ተደራሽነት ማስፋፋት፣

### የሥራ ዝግጁነት በአሃዝ

**28** ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከሥራ ዝግጁነት ፕሮግራሞች

**34** የሥራ ዝግጁነት ፕሮግራሞች ጥናት

**12,871** ለሥራ ዝግጁነት ኮርሶች በ2015 - 2016 የትምህርት ዓመት ተማሪዎች ምደባ አግኝተዋል

**26.5%** ስለሥራ ዝግጁነት በከፊል የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ይሳተፋሉ

ትምርት አካደሚ/Career Readiness Education Academy (CREA) 21 ዓመት እድሜ ከመሙላታቸው በፊት ለመመረቅ የሚጠበቅባቸውን ለመጨረስ የማይችሉ ተማሪዎችንና ውስን ወይም መደበኛ ትምህርት የተቋረጠባቸውን ተማሪዎች ለመርዳት ነው።

ለተማሪዎች የሚሰጥ ድጋፍ የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ወደ ስኬታማነት ደረጃ ተማሪዎቻችንን ለመደገፍ ቁርጠኝነት አለው። እንደነዚህ ባሉት.ፕሮግራሞች ላይ የእኛ ኢንቨስትመንት *በቁጥር አናሳዎቹን ምሁራን የላቀ ምሁራዊ ችሎታ እና ስኬታማነትን ለማዳበር/Achieving Collegiate Excellence and Success (ACES)* በዘልማድ ተገቢ ውክልና ካላገኙት ማህበረሰቦች የሚመጡትን ተማሪዎች መምከርና ማሠልጠን ለፈተና ማዘጋጀት እና ይመለከተኛል የሚል ስሜት ለማዳበር ነው።

# ዓላማ ላይ የተመረኮዙ የማስተማር ስልቶች

የተዋጣለት የተማሪን ትምህርት ዒላማ ያደረገና በእውቀት የሚሰጥ ማስተማርን ይጠይቃል። ይህ የሚጠይቀው ከጥቅል ዳታ/ቁጥር ያለፈ ደረጃን የሚመጥን ቴስት-ፈተና እና ስለ እያንዳንዱ/ዷ ተማሪ

- ይህ ተማሪ እየተማረ ነው? ይህች ተማሪ እየተማረች ነው?
- በቂ ትምህርት/ዕውቀት እየቀሰሙ ናቸው?
- እንዴት እናውቃለን?
- እየተማሩ ካልሆነስ፣ ለምን?
- ስለዚህ ምን ማድረግ ይኖርብናል?

## ዳታ/ቁጥር ብልጭታ ነው።

ቁጥር/ዳታ አንድን ተማሪ አይገልጽም፣ ነገር ግን አስተማሪዎችን ተማሪው/ተማሪዋ ምን ያክል እየተማረ/እየተማረች እንደሆነ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። ይህንን ለማድረግ ስለተማሪው/ስለተማሪዋ የመማር ሁኔታ ለመወሰንና ለውጥ እያደረጉ መሆናቸውንና ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልገውስ የቱ ጋ እንደሆነ በርካታ አቅጣጫዎችን/እርምጃዎችን መመልከት ይጠይቃል። እነዚህ እርምጃዎች የሚያካትቱት ቴስቶችን፣ ፈተናዎችን እና የክፍል ደረጃን የሚመጥን ድርሰት መጻፍ፣ እና ደረጃ የሚመጥን በስቴት ደረጃ የሚሰጥ የቴስት ዳታ/መረጃ ነው። አዲስ የመረጃ መገልገያዎችን በመጠቀም፣ መምህራን የተማሪዎችን አሠራር የበለጠ ክትትል ለማድረግና አስፈላጊ የሆነ ድጋፍ ለመስጠት ወይም የተማሪዎችን ፍላጎት ለማሳካት ይበልጥ ሊያሠሯቸው ይችላሉ።

## በብቃት የማስተማር ባህል ያላቸው


የሰው አዕምሮ በተቻለ መጠን ውጤታማ ለመሆን መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማዋሃድ አቋራጮችን ይወስዳል። ያለመታደል ሆንና፣እነዚህ አቋራጮች አንዳንድ ጊዜ ያለአስፈላጊ የሆነ ማዘንበል እና የጅምላ አመለካከት ይፈጥራሉ። ለሚያስተምሩ፣ ይሄ ሊያመራ የሚችለው ተማሪዎችን ከችሎታቸው ይልቅ በዘር፣ በጎሳ፣ ወይም በፆታ፣ ተመስርቶ ይሆናል ብለው እንዲጠብቁ ያደርጋል። ይህንን ውስጠታዋቂ/ጥርጥር የሌለው አድልዎ ለመፋለም እና መምህራን ከየትኛውም ወገን ተማሪዎች ጋር የተሻለ ግንኙነት እንዲኖራቸው MCPS የግዴታ መወሰድ ያለበትን የብቁነት ስልጠና ለሁሉም መምህራን አዘጋጅቷል።

## የእኛን ተማሪዎች ማንጸባረቅ

የተማሪ ውጤት የሚጨምረው ተመሣሣይ መነሻ/ልምድ ያለው/ያላት መምህር/መምህርት ት/ቤት ውስጥ ሲገኝ መሆኑን ጥናቶች ያለመለክታሉ። እያደገ የመጣው የእኛ ተማሪዎች ስብጥር አካል ከተለያየ መነሻ የመጡ ጥራት ያላቸው አስተማሪዎችን የማግኘት እድል እንዲኖራቸው ለማረጋገጥ MCPS በተለየ ትኩረት ከብዙ ስብጥር የሚያመለክቱትን በመመልመል እያበረታታ በእኛ የትምህርት ሲስተም አስተማሪዎች እንዲሆኑ ይጥራል። በተጨማሪም በርካታ ስብጥር ረዳት ባለሙያዎችን ወደ ሰርቲፋይድ መምህርነት የሚያድጉበትን መንገዶችን እየፈጠርን ነው።

## ቤተሰቦቻችንን መርዳት/መደገፍ

ተማሪ መማሪያ ክፍል ውስጥ ትምህርት ሲጀምር ቤት ውስጥ ይቀጥላል። ለዚህ ነው MCPS ባለው የበርካታ ቋንቋ ተናጋሪዎች የወላጅ እና ማህበረሰብ አስተባባሪ ቡድን እና የተማሪ ሠራተኞች አማካይነት ድጋፍ ለመስጠትና መጠቀሚያዎችን/resources በመለየት ለቤተሰቦች ለመስጠትና ድጋፍ ለማድረግ ቁርጠኝነት የሚኖረን። በተጨማሪም እንግሊዝኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ላልሆነ ቤተሰቦች ወቅታዊ የሆነ የትርጉም ሥራ እና የማስተርጎም አገልግሎቶችን ለመስጠት ኢንቨስት ማድረጋችንን እንቀጥላለን።



ዋነኛ እሴቶቻችን ትምህርት፣ ግንኙነቶች፣ መከባበር፣ ልቀት፣ ፍትሃዊነት።

## K-12 ወሳኝ የጉዞ ምዕራፍ

ዝግጁነት፡- 12ኛ ክፍል

ዝግጁነት፡- 11ኛ ክፍል

ሁለተኛ ደረጃ (9 - 12) ሁሉንም በአንድነት መሳብ፣ የትምህርት ይዘት ማስፋፋት፣ ችግር/ፕሮብሌምን ለመፍታት እውቀትን እና ሙያ/ችሎታን፣ ትንተና፣ እና ቅንብር ለኮሌጅ እና ለሙያ ትምህርት ዝግጅት ማቀናጀት።

ስኬታማ ሽግግር ፡ ክፍል 9

ዝግጁነት ፡ ክፍል 8

መካከለኛ ደረጃ (6 - 8) - በንባብና ጽሑፍ እና ሂሳብ እንዲሁም እነዚህን ችሎታዎች ወደ ሌሎቹም የትምህርት ይዘቶች ማስፋፋትን በጥልቀት መተግበር።

ስኬታማ ሽግግር ፡ ክፍል 6

ዝግጁነት፣ ክፍል 5

መካከለኛ (3 - 5) የትምህርት መርጃዎችን በመጠቀም የመረዳት ችሎታ/ዕውቀት፣ ስሌት/ሂሳብ፣ ግንኙነቶች/ተግባቦት

ስኬታማ ሽግግር፣ ክፍል 3

ዝግጁነት፣ ክፍል 2

የመጀመሪያ መሰረታዊ መነሻ (K-2) - ስለ መሠረታዊ የትምህርት መርጃዎች ማወቅ፣ ማንበብ፣ መጻፍ፣ እና ማስላት።

ስኬታማ ሽግግር፣ ክፍል K

ደረጃውን የሚላላል/ታሚላለችለውጥ/እድገት እያሳየ(ች) ነው


## የተመረቁ ተማሪዎች ብዛት:

| ንዑስ ቡድኖች | 2016-2017 COHORT |
|---|---|
| ሁሉም ተማሪዎች | 10,233 / 89.5% |
| ኤዥያውያን | 1,561 / 97.3% |
| ጥቁር ወይም አፍሪካዊ አሜሪካዊ | 2,245 / 88.2% |
| ሂስፓኒክ/ላቲኖ | 2,477 / 78.5% |
| ነጭ | 3,515 / 96.0% |
| ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ዘሮች | 417 / 93.3% |
| ልዩ ትምህርት | 830 / 69.5% |
| *የእንግሊዝኛ ችሎታቸው ውስን የሆነ (Limited English Proficient) | 280 / 40.7% |
| ነፃ እና የቅናሽ ዋጋ ምግቦች (FARMS ) | 2,457 / 81.9% |


ማሳሰቢያ፡- አሜሪካን ኢንድያን ወይም የአላስካ ተወጅ ተማሪዎች እና የሐዋይ ወይም የፓስፊክ ደሴቶች ተማሪዎች ሁሉም ተማሪዎች በሚለው ቡድን ውስጥ ተካተዋል ነገር ግን ለየብቻቸው ሪፖርት አልተደረጉም።
በመመረቂያ ወቅት የእንግሊዝኛ ችሎታው(ዋ) ውስን ነው

## AP/IB ኮርስ ምዝገባ

### % በ AP/IB ኮርሶች የተመዘገቡ





## የ AP ፈተና ውጤት/አሠራር




ማሳሰቢያ፡- AP = ከፍተኛ ደረጃ ምደባ፣ የ AP ፈተና ውጤቶች በሴፕቴምበር 2017 የኮሌጅ ቦርድ ሪፖርትን ተመርኩዞ ነው።


## PARCC አልጀብራ I ተሳትፎ፡-

### የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች




## PARCC አልጀብራ I ውጤት (3 ወይም የበለጠ)

### 8ኛ ክፍል




የበለጠ መረጃ ለማግኘት፡- www.MontgomerySchoolsMD.org/all ይጎብኙ።